“ተነሥተንም ወደ ቤቴል እንውጣ በዚያም
በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ በሄድኩበትም
መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው ለእግዚአብሔር
መሰውያን አደርጋለሁ።“ ያዕቆብ በኦዘፍ.ም 35ቁ.3-4

## <u>ወጣ ወደ ቤቴል</u>

ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን
በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን
ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን
የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።

በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ አርባ ሦስት
የያዕቆብን ክብር እንዲህ ተረዳሁት።
ለእስራኤል ዘመንፈስ ያዕቆብ አባት ነህ
ልትሰበስባቸው አምላክ የላከህ።
ሰዎች ለናቋቸው ለተጠሉ ሕዝቦች
ሽክማቸው ለበዛ ባርያ ለገገሮች።
እስከ አለም ዳርቻ ለተበተኑት
ተመርጠሀል አንተ ለዳግም ምዕአት።

ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን
በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን
ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን
የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።

ለቃሉ የቆመ በዕምነቱ የፀና
ከሚሊዮኖች ውሰጥ የተገኘ ጀግና።
ቢፈራረቁበት ጥፊና እርግጫ
ጨለማ ቢከቱት ቢያበዙበት ጡጫ።
ፍጹም ያልታጠፈ የእውነት አርበኛ
ሙሉነህ እዩኤል ኮራንብህ እኛ።
የኢትዮጵያ ልጆች የእንባቸው ውጤት
ጌታ ያዘጋጀው ፍቅር ነው ቅንጅት።

ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን
በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን
ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን
የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።

በአስቻለው ከተማ እንግልትና ሞት
ተወገደ ዛሬ የ እኛ ፍርሀት
ቀና አለች ኢትዮጵያ ከጎበጠችበት
ኃይሉ አርአያ ሆኗት ለዕምነቷ ፅናት።
ግዛቸው ሕዝቦቿን ተዘረጋ እጃቸው
ምስጋና አቀረቡ ዛሬ ለአምላካቸው።

ኢትዮጵያን ተመልከት ቃል ኪዳንህን
የእውነቱ ጌታ ብርሀኑ መስፍን።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

ሕፃናት ቦረቁ በዚያ ደስታቸው
የብርቱካን ፍሬ ወተት ሆኖላቸው።
በምስራቅ ምዕራብ መአዛው አየሩ
ብርቱካን ብርቱካን ሸተተ አገሩ።
የቅንጅት መንፈስ ፍቅርና ሰለም
እንግዲህ ከኢትዮጵያ ብርሀኑ አይጠፋም።
ይህን ለፈቀደ ብሩክ መስፍናችን
ወጣን ወደ ቤቴል ይድረስ ምስጋናችን።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

ግዛቸው ተብሎ ለእኛ የተሰጠን
የቅንጅት መንፈስ አንድ አደረገን።
ብሩክ ነው ጌታችን የፍቅር አምላክ
አርበኛውን ክፍሌ ለእኛ የሚልክ።
መስዋዕት የሆኑ እንደ ሐዋርያት
ቅንጅቶች ናቸው የነፃነት መብራት።
ይጠረግ መንገዱ የጎበጠው ይቅና
የኢትዮጵያ ምዕአት ጊዜው ቀርቧልና።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

አባይነህ ተስፋችን ከርሀብ እምንወጣበት
ኃይሉን እንጠቀም ለተፋጠነ ዕድገት።
ኢትዮጵያ ትላለች አባይ ተመለስ
የምድሪቷን አፈር ይቅር ማጋበስ።
አስተማርከን ስደት ለሰው ቤት ማደርን
ዕዉቀትና ጉልበት ገብሮ መኖርን።
ፊታችን ይመለስ ይሁንልን ምዕአት
ከመቃብር አምባ ኢትዮጵያን እናንሳት።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**

**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

ካናዳ አዉሮፓ እንዲሁም አሜሪካ
ሐዋርያት ወጡ ገሰገሱ አፍሪካ።
ፍቅርና ሰላም ለራበው በስደት
ሊሰብኩት ነጎዱ ውጤቱን የአንድነት።
ፍቅርና ሰላም የሚዘራ በአለም
ቅንጅት መንፈስ ነው የምዕአት መቅድም።
ቀረበ ፍፃሜው ትንቢተ ኢሳይያስ
ሊጎበኘን ጌታ እንባችን ሊታበስ።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

በዳዊት መዝሙር በሰለሞን ጥበብ
እንድአርጋቸው ብሎ ሕዝቡ ሲረባረብ።
ግራ ቀኝ ጨልሞ ታግተው አርበኛች
ሰይጣን ሲከፋፍል  የኢትዮጵያን ልጆች።
የብብት ውስጥ እሳት እየለበለበን
ስድብ ውርደታችን እያንገበገበን።
በፅናት አቁመህ የሰጠኸን ሞገስ
ብርሀነ መለኮት ስምህን ላወድስ።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

ተሰወረባቸው አጡ ማስተዋልን
የብርሀኑ ጌታ ለእኛ ያረገውን
ጠረጠሩ ኃይሉን አምላከ ያዕቆብን
የሰላም የፍቅር የእውነት መንፈስን።
ሄዱ ገሰገሱ የይሁድ ቅሪቶች
ሊበሉ ሊጠጡ ከነፍሰ ገዳዮች።
ሊሳከሩ ሄዱ ሊሉ ሚሊኒየም
ይቅር ሳንባባል ሳይጠራ የሰው ደም።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

በልቤ ውስጥ ያለ የተዳፈነ እሳት
ትንፋሼ አቀጣጥሎት እንዳይሆነኝ ጉዳት።
የብብቴ ውስጥ ፍም በጉያየ ያለህ
ትናንት ያስቀየምከኝ የዛሬው ያልታየህ።
አውቀህም ሳታውቀው ትግሉን ያጓተትከ
በመሰሪ ተንኮል የተወናበድክ።
ይቅርታም ለምድር ንሰሐም ለጌታ
አስታራቂ ናቸው ዛሬን አታመንታ።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

ልጅየው ሰለሞን አባትየው ዳዊት
ጌታን ሲያወድሱ ሆነው በቅንጅት።
ዳዊት በክራሩ ሲል አንድአርጋቸው
ብርሀነ መለኮት ሞገስን ሰጣቸው።
የእምነትን ዕዳ ጠብቀው ቃልን
በጎቹን በአንድነት የአሰባሰቡን።
ያዳኑን ከተኩላ ከነጣቂ አሳቾች
ዛሬ ይመስገኑ የቁርጥ ቀን ልጆች።
ዛሬ ይመስገኑ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች
ለእምነታቸው ሟቾች።

**ወጣ ወደ ቤቴል ያዕቆብ ሊያመሰግን**
**በመከራው ጊዜ ብርታት የሰጠውን**
**ብርሀኑ ፈንጥቋል አይተነዋል ኃይሉን**
**የያዕቆብን አምላክ ውጡ እናመስግን።**

በቅንጅት ዙርያ ለተሰባሰቡ ለኢትዮጵያ መስዋዕት ለከፈሉ፣ ትግሉን ላፋፋሙ፣ በፅናት ለቆሙ፣ በገንዘባቸው፣ በጉልበታቸውና በእውቀታቸው ሁሉ አስተዋጽኦ ለአደረጉ የኢትዮጵያ ልጆች መታሰቢያ የተዘጋጀ።

ተፃፈ ስዊዘርላንድ - በርን- 12.08.2007
የአጽብአሔ